DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

# SY24-25 የ'PHELPS የምህንድስና (Architecture)፣ የግንባታ እና የኢንጂነሪንግ (Construction, and Engineering) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የመግቢያ ሂደት የደረጃ መጠን (Admissions Process Rubric)

ለክፍል ደረጃዎች፡ 9-11

**ስለ 'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመግቢያ (Admissions) መስፈርት:** በ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ችግሮችን የሚፈቱ፣ በስራ መስክ የቴክኒካል የትምህርት ፕሮግራማችን ላይ ፍላጎት ያላቸው፣ እና መፍትሄን ለማግኘት ሲባል ፈታኝ በሆኑ ነገሮች ውስጥ ለመስራት ፈቃደኛ የሆኑ ምሁራኖችን ማግኘት እንፈልጋለን። ምንም እንኳን የውጤት ደረጃቸው ወይም ያስመዘገቡት ውጤቶች ምርጥ ነው ባይባልም እንኳን፣ በክፍል ስራዎቻቸው ላይ ጥረት የሚያደርጉ፣ በይበልጥ ስኬታማ የሆኑ አመልካቾችን እንፈልጋለን።

**ስለ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመግቢያ (Admissions) ሂደት:** በ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ፣ የመግቢያ (admissions) ሂደታችን የሚያካትተው፣ ጽሁፍ (essay)፣ ቃለ-መጠይቅ፣ እና ሁለት የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations)ን በMy School DC ማመልከቻ አማካኝነት ማስገባት ነው። ለእያንዳንዱ እጩ፣ እያንዳንዱን የመግቢያ (Admissions) ክፍሎችን ከግምት ውስጥ የምናስገባ እና ሁሉም አመልከቾች አንድ ዓይነት በሆነ የደረጃ መጠን (rubric) ይመዘናሉ። ምንም፣ አንድ-ብቻ የሆነ የመግቢያ (admissions) ክፍል፣ ብቻውን ለብቁነት መወሰኛ ሆኖ አይወሰድም። ሁሉም ተማሪዎች፣ ለመግባት (admission) ብቁነታቸው እንዲታይላቸው ከግምት-ውስጥ እንዲገቡ ለማድረግ፣ የቃለ-መጠይቅን ማጠናቀቅ አለባቸው።

እያንዳንዱ ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሠረት የደረጃ ውጤት (scored) የሚሰጠው እና የሚመዘን ይሆናል።

| የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች | መለኪያ (Weight) | ማስታወሻዎች |
|---|---|---|
| የቀለም ትምህርት የመስፈርት ምልከታ (GPAን እና በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት/attendance የሚያካትተ) | 40%<br>(12/30 ነጥቦች) | የ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የውጤት (GPA)ን እና በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance)ን፣ እንደ የቀለም ትምህርት የመስፈርት ምልከታ ይመለከተዋል። ምንም ዓይነት፣ በአነስተኛነት የሚጠበቅ (minimum) GPA እና በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) መለኪያ አያስፈልግም፣ ነገር ግን ሪፖርት ካርድ መግባት አለበት።<br><br>በተለምዶ፣ በፕሮግራማችን ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች የ2.5 GPA (የሚመከር/recommended) ወይም ከዚያ በላይ እና የ90% ወይም ከዚያ በላይ በክፍል ውስጥ መገኘት (in-seat attendance) ያላቸው (የሚመከር/recommended) ሲሆን፣ ሆኖም፣ አነስተኛ GPAዎች ያሏቸው ተማሪዎች፣ ትክክለኛ የሆነ እርዳታን እና ስልቶችን ሲያገኙ ስኬትን ማግኘት እንደሚችሉ ማወቅም ችለናል። |



1200 First Street, NE | Washington, DC 20002 | T 202.442.5885 | F 202.442.5026 | dcps.dc.gov

| | | |
|---|---|---|
| ቃለ-መጠይቅ | 40%<br>(12/30 ነጥቦች) | የ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በፕሮግራማችን ላይ ፍላጎት ያላቸውን፣ እና ችግሮችን ለመፍታት ፈቃደኝነትን የሚያሳዩ ተማሪዎች ለመለየት ጠንካራ እምነት አለው። የወደፊት ተማሪዎቻችንን ለመተዋወቅ የምንፈልግ እና ይህንንም ለማድረግ የቃለ-መጠይቁ ጠቃሚ መንገድ ነው።<br><br>ተማሪዎች ወደ ቃለ-መጠይቁ፤ ከቤተሰብ አባል ጋር (ከወላጅ፣ ሕጋዊ አሳዳጊ፣ ወይም ከሌላ የቅርት የቤተሰብ አባል) ወይም ሌላ በህይወቱ ውስጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ያለው ሰው ጋር (እንደ አሰልጣን፣ አማካሪ፣ ወይም የሕይወት መሪ/mentor)፤ ተማሪዎችን በመደበኛነት ከሚረዷቸው ጋር አብረው እንዲገኙ እንጠይቃቸዋለን።<br><br>በተማሪው የቃለ-መጠይቅ ወቅት፣ አብሮ-የሚመጣው አዋቂ-ሰው የትምህርት-ቤት ጉብኝትን ማድረግ የሚችል ወይም በጥያቄና-መልስ (Q&A) ክፍለጊዜዎች ውስጥ ከተማሪ አምባሳደሮች እና/ወይም የ'PTO' አባላቶች ጋር መካፈል-የሚችል መሆን አለበት።  አብሮ-የመጣው አዋቂ-ሰው ያለው ተሳትፎ፤ በውጤት-አሰጣጡ ላይ በማንኛውም መንገድ ቦታ-የሚሰጠው አይደለም።<br><br>በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY24-25 ውስጥ፣ የቃለ-መጠይቁ በርቀት (virtually)፣ ሊከናወን ይችላል። የጤና መመሪያን በመከተል እና በመቆጣጠር ላይ፣ ቁርጠኛ ሆኖ መስራቱን - DCPS ይቀጥልበታል። |
| በቦታው-ላይ የሚከናወን የመጻፍ ናሙና/On-Site Writing Sample (በቃለ-መጠይቁ ወቅት የሚጠናቀቅ) | 10% ( 3/ 30 ነጥቦች) | ልክ እንደ ቃለ-መጠይቁ፣ በፕሮግራማችን እና በጽሁፍ ንግግር (communication) ችሎታዎች ላይ፣ የተማሪው ፍላጎት ምን እንደሆነ ለማወቅ፣ የጽሁፍ ሃሳብ ማቅረቢያው (writing prompt) - ጥቅም-ላይ ይውላል። ይህ ሃሳብ-ማቅረቢያ (prompt)፣ እንደ የቃለ-መጠይቁ አካል-ሆኖ - በቦታ-ላይ ይጠናቀቃል።<br><br>የጽሁፍ ሃሳብ ማቅረቢያዎች (Writing prompts)፤ ለሁሉም አመልካቾች ጥቅም ላይ በሚውለው ውስጣዊ የደረጃ መጠን (rubric)፣ ለተማሪውን የብቁነት የውጤት ደረጃ (score) ሲቆጠር፣ 10% በሆነው የጽሁፍ ውጤት ደረጃዎቹ ላይ የሚገመገም ይሆናል። ምንም እንኳን ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ  ትምህርታቸው ወቅት በሙሉ አዘውትረው መፃፍ ቢጠበቅባቸውም፣ ለሃሳብ-ማቅረቢያ (prompt) የደረጃ መጠኑ (rubric)፣ በቴክኒካል የአፃፃፍ ችሎታዎች ላይ፤ እንደ ሰዋሰውና ቃላት (grammar and vocabulary) ላይ ያተኮረ አይሆንም።<br><br>በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY24-25 ውስጥ፣ የጽሁፍ የሃሳብ-ማቅረቢያዎቹ (writing prompts) በርቀት (virtually)፣ ሊከናወን ይችላል። የጤና መመሪያን በመከተል እና በመቆጣጠር ላይ፣ ቁርጠኛ ሆኖ መስራቱን - DCPS ይቀጥልበታል። |

| | | |
|---|---|---|
| የድጋፍ መስጫዎች (Recommendations) | 10% ( 3/ 30 ነጥቦች) | የ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የተማሪውን የትምህርት ቤት ውስጥ ተሞክሮ የበለጠ ለመረዳት እና ለሪፖርት ካርዳቸው ይዘትን ለመስጠት በማለት፤ የአስተማሪን ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) ይጠቀማል።<br><br>ሁለት ድጋፍ መስጫዎች (recommendations) እንዲቀርቡ እንጠይቃለን። በተጠየቀው አስተማሪ አንድ ብቻ ተሞልቶ ከተጠናቀቀ፣ በገባው አንድ ድጋፍ መስጫ (recommendation) ላይ መሠረት በማድረግ ተማሪውን እንገመግማለን። ምንም ዓይነት ድጋፍ መስጫ (recommendations)ን ካላስገቡ፣ ትምህርት ቤቱ የ10% መጠን (weight) ወደ ቃለ-መጠይቁ ይጨምራል። |
| **በተለምዶ፣ በደረጃ መጠን (rubric) 15 ወይም ከዚያ በላይ ያመጡ ሁሉም ተማሪዎች ብቁ የሚሆኑ ሲሆን፣ ይህ በአነስተኛነት የሚጠበቀውን (minimum) የውጤት ደረጃ፣ በየዓመቱ ለእያንዳንዱ አመልካች፣ ሁሉን አካታች በሆነ ምልከታ አማካኝነት ወደ ዝቅተኛ ደረጃ የሚስተካከልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። በአነስተኛነት ከሚጠበቀው (minimum) የውጤት ደረጃ በላይ ያመጡ ሁሉ አመልካቾች ብቁ ይሆናሉ፤ እንዲሁም አመልካቾች በተጠራቀመው የደረጃ መጠን (rubric) መሠረት አድርጎ በተከተለ አሰራር ደረጃ እንዲያገኙ ይደረጋል።** | | |